# <u>**የጀግኖች ስም በፀረ ኢትዮጵያዉያን ሲጎድፍ(ከአሸብር)**</u>

ወላጆቻችን እንዲህ ዓይነቱ አወዛጋቢና አደናጋሪ ቅጥፈት በማያዉቀዉ ቦታና ታሪክ ገብቶ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚል ሰዉ ሲያዩ። ወይ ግዜ ከንቱ እያሉ የዉስጥ ብሶታቸዉ በቁጭት ይገልፁ ነበር። እረ ለመሆኑ መች ይሆን ረጋ ብለን ጠቃሚ ትምህርት ሰጭ፣ ገንቢ ተግባራትና እርቀ ሰላም በህዝባችን ላይ ሊያመጡለት የሚችሉትን ምክሮች በቀና መንፈስ መስማት ለሚፈልገዉን ማቅረብ የምንችለዉ ።

ስድብ ስድብን ይወልዳል እንጅ ፍቅርን አይገዛም። ስለዚህ ለምን ይሆን ገና አንድ መስመር ባልሞላ ፅሁፍ ቡራካኪ ማስማቱና ጣት መቀሰሩ አገራችን ለገባችበት ኪሳራና ዉድቀት ጥቅሙ ከምኑ ላይ ነዉ። ጎበዝ ወደ ኋላ ዘወር ብለን ታሪካችን መቃኘቱ በይበልጥ ጠቃሚነቱ ይታየኛል። ይህ ስልም ባለፉት ታሪኮቻችን ስህተቶች አልተሰሩም**(አልጋ ባልጋ ነበር መንገዱ)**ለሁሉም ማለቴ እንዳልሆነ መጠቆም እወዳለሁ ። መልካም ዓርአያ ሰጭ የሆኑትን ባህሎቻችን አክብረን ስንይዝና ጎጅ የነበሩት ባህሎቻችንም ማረምና ማስተካከል ሲገባን እንዲህ ሲባል ነበር ተብሎ ብስሉና ጥሬዉን በአንድ መዉቀጫ አስገብቶ መዉቀጡ ትልቅ የታሪክ ክስረት ነዉ ። ሥለዚህ ጥፋት ያጠፋዉን ወገን ከስህተቱ ተምሮ ቀና መንገድ እንዲዝ ለማድረግ ማግባባትና ማቀራረብ ሲገባ እንደ የኔዉ ብጤ ለማኝ ለምኖ ገንዘብ ሳይሰጠዉ ሲቀር የስድብ ናዳ እንደሚያወርደዉ የእንካ አሰለንትያ አይነቱ ንትርክ አድማጭም ተቀባይነትም አይኖረዉም። ጠቃሚነቱ አፍነዉና ረግጠዉ ለሚገዙን አምባ ገነኖች ብቻ ነዉ።

ሁሌም ጭንቅላቴ ዉስጥ ሆኖ እረፍት የነሳኝ ነገር ቢኖር ሞትን ያክል አስፈሪ ነገር የማይፈራዉን ትዉልድ ለአገር ክብር፣ለአንድነት፣ለዲሞክራሲና ለፍትህ መጓደል ሲሉ እንደ ሻማ ቀልጠዉ ያለፉትን ብርቅዬ የኢትዮጵያ አርበኞች ታሪካቸዉ ተገልብጦ ሲፃፍና የከፈሉት ከባድ የጀግንነትን ዋጋ ትርጉሙ ምን እንደሆነ በማያዉቁ በዛ ቀዉጢ ዘመን የት እንደነበሩ የማይታወቁ የወረቀት ነብሮች በቃችሁ መባል ይገባቸዋል። እየሰማን ዝምታን የወደድነዉ ነገሩ አጥተነዉ ሳይሆን ለአተላዮችና መሰሪዎች መደንፍያ ቀዳዳ ላለመፍጠር ስንል ነዉ።

የአቶ ሮዛ አባድሪን ጥላቻን የተመረኮዘ ፅሁፍ በ10-06-2011 በECADF ድህረ ገፅ ላይ ኢሕአፓን የሚኮንን ፅሁፍ ሳይ ትዝ ያለኝ ነገር ቢኖር በምኖርበት አካባቢ ባልሳሳት የፋሲካዉ ወራት አካባቢ ከአንድ ጓድኛየ ቤት ተጋብዠ ሕጂ የሰማሁት ቅሌት ልክ እንደ አቶ ሮዛ አባድሪ ሰዉ ሰራሽ በሬ ወለደ አይነቱ ስድብ ስለሚያጠናክረዉ ነዉ ማዉሳት የተገደድኩት። ግብዣዉ እንዳበቃ እንደተለመደዉ ስለ አገር ጉዳይ ተነሳና ውይይት(ንትርክ)ተጀመ ። ከነበርነዉ መካከል አንድ ብቻ ነዉ ያለዉን መንግስት መዉቀስ የማይፈልገዉ ምክንያቱም ያሰራት ኮሳሳ ቤት ይወስዱብኛል ብሎ ስለ ፈራ መሰለኝ። ሌላዉ ግለሰብ ግን ኢሕአፓን አያዉቀዉም እንደሰማሁት ብሎ ያቀረበዉ አስተያየት ኢሕአፓ አጠቃላይ አባሎቹ ከአስራ ስምንት አይበልጡም እነሱም አርጅተዉ መንቀሳቀስ እየተሳናቸዉ ነዉ ። ነገር ግን እነሱን የሰጠ ምላስ ፈጣሪያችን ለማንም አልሰጠም። መሪያቸዉም እያሱ ይባላል ከወያኔ ጋር እጅና ጓንት በመሆኑ መለሰ ዜናዊ በወር $5000ዶላር እየከፈለዉ ወያኔ

በስልጣን እንዲቆይ የሚፈልግ ህቡዕ የካቢኔ አባል ነዉ። ዋናዉ ተግባሩ በOLF/እና G-7 እየተካሄደ ያለዉን ድርድር እንዲያኮላሽ የቤት ስራ ተሰጥቶት የሚሰራ ነዉ ። እኔም የሰዉዬዉ የፖለቲካ ብስለት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ በሰዉየዉ አልፈርድም። ይህን እንዲናገር የገፋፋዉ ድርጅት ይሁን ግለሰብ ግን ምንኛ የከሰረ እንደሆነ እዚህ ላይ ለሁሉም ግልፅ መሆን አለበት።

በመጨረሻም የሰጡሁት መልስ የሰማ ሰዉ ይስቅብሃል። ይህን የማይታመን ወሬ የነገረህ አንተነትህን ዝቅ አድርጎ እንዲገመገም አድርጎታል ስለዉ አዬ እኔ የፖለቲካ ሰዉ አይደለሁም ነገር ግን በአካባቢዬ ሰላም ተፈጥሮ ማየት ስለ ምኻ አልስማማም ያለዉን ድርጅት የጠላሁት ብሎ አለኝ። ለነገሩ ግለሰቡ በዘመናዊ ትምህርት የፋርማሲ ባለ ሞያ ነዉ። ደቡብ ኢትዮጵያ የተወለደ መአከላዊ እድሜ ያለዉ ወጣት ነዉ። ይህን ካልኩ በኋላ ወደ ተነሳሁበት አርዕስት ልመልሳችሁ።

***አቶ ሮዛ አባድሪን** ጥላቻና ዉሸት እንዲቀስሙ ያሰለጠናቸዉ ማን ይሆን? በማያዉቁት ታሪክና ነገር ገብተዉ በል ተብለዉ ያናፈሱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ልብ የገዙ እለት ሳያሳፍራቸዉ አይቀርም እዉነት የድርጅት ሰዉ ካልሆኑ? ምክንያቱም የማንም ድርጅት ደጋፊ አይደለሁም ብለዉ ሲያበቁ ነገር ግን የድርጅት ስም እየጠቀሱ መሪዎች ነን ከሚሉት በላይ ነዉ ያጉራሩት ።

የኢህአፓ ጀግኖች ሰማዕታት ለኢትዮጵያ ክብርና ሕልዉና ፣ለሕዝቦችዋ ዲሞክራሲያዊ መብት ሲሉ ለጋዉ ሂወታቸዉ መገበራቸዉ የሚያዉቀዉ ኢትዮጵያዊዉ የሆነ ወገን እንጅ ለጥፋት የሚያስቧት በታኝ ጠላቶችዋማ ያልነበረ ታሪክ እየጻፉ ስም ከማጉደፍ አልፈዉ ሌላ የሚሉት ነገር እንደለለ የማያዉቅ እዉነተኛ ኢትዮጵያዊ አለ ብየ አላምንም ። አቶ እያሱ አለማየሁ የተባሉ የኢህአፓ የበላይ አመራር አባል ስላለዉ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ኢሕአፓን አስመልክቶ መሠረቱ በስዊድን አገር የሆነ የአንድነት ራድዮ ያቀረበላቸዉ ጥያቄዎችና መልሶች ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ አዳምጬዉ አለሁ። እንደ እኔዉ ግምገማና አስተያየት ግለሰቡ ስለኢሕአፓ ታሪክ በአጭሩ ከመወለዱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያደረገዉ ትግል እስከነ ድክመቱና ጥንካሬዉ ሁሉም ሊረዳዉ በሚችል አገላለጥ መስማት ለሚፈልገዉ ኢትዮጵያዊ ግልፅ አድርገዉ አቅርበዋል ከምኑ ላይ ነዉ ዉሸቱ?

አቶ ሮዛ ከፃፉት ፅሁፍ እንደገለጹት የዛ ትዉልድ አባል አይደለሁም የማንም የፖለቲካ ድርጅት አባልም አይደለሁም ካሉ ማን ያዉራ የነበረ እንጅ ያልነበረ የለለዉን ታሪክ ባዶ ሜዳ ላይ ሆኖ መጮሁ ለምን አስፈለገ። እኔ ያሳመመኝ ከአቶ ሮዛ በበለጠ በእዉቀት የደረጁና የበሰሉ አባረዉ መፃፍና ማስረዳት ይችሉ የነበር ለእነ አቶ ሮዛ የነፃነት ብርሃን ለማብራት ሲሉ ሞተዉ አፈር ለተጫናቸዉ ጀግኖች በኢሰፓ፣በሻዕብያና በወያኔ አደናጋሪ ጭብጥ በለለዉ ፕሮፖጋንዳ የሰከሩ ግለ ሰዎች ሲወቀሱ መስማት ስለማልፈልግ ነዉ ይህችን አጭር መልስ ለመፃፍ የተገደድኩት እንጅ የአቶ ሮዛ የቆጡ- የባጡ የጥላቻና የስም ማጥፋት ትረካ ለዉጥ ያመጣል ብዬ አይደለም። ነገር ግን ዉሸት ተደጋግሞ ሲነገር ብዙ የዋሆችን እንዳያደናግር ለማስጠንቀቅ ያስተላለፍኩት መልዕክት

ነዉ።

ኢሕአፓ በኢትዮጵያ አንድነት፤ልዓላዊነቷ፤ደንበሯና ታሪኳ የማይደራደር ሃቀኛ ድርጅት በመሆኑ በጠላቶቹ ለብዙ ዓመታት የተሰነዘረበት የማጥፋት ዘመቻ ተቋቁሞ ትግሉን አድሶ ቀጠለ እንጅ ለቆመለት አላማ አንድ ስንዝር እንኳ ወደ ኋላ ብሎ አያዉቅም። አሁንም ቢሆን በጥፋት ሃይሎች እየተካሄደበት ያለዉ ጥንቆራ ከምንም ሳይቆጥር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባለትን ቃል ተግባር ላይ ሳያዉል አርፎ አይተኛም። በዚህ ሳምንት የታዘብኩት አስገራሚ ነገር  በእስራኤልና በፍልስጤም መካከል የተካሄደዉ ስምምነት አንድ የእስራኤል ወታደር በአንድ ሺ ሁለት መቶ ፍልስጤማዉያን እስረኞች ልዉዉጥ ተደርጓል ። ከዚህ የምንማረዉ ነገር ቢኖር የዓላማ ጥንካሬን እንጅ የቁጥር ማነስ ወይም መጉደል የጀመርከዉ ጉዞ አያዛባዉም እንግዲህ ኢሕአፓም እንደተባለዉ 18 አባላት ብቻ ቢኖሩትም ጥንካርያቸዉ ግን በሚሊዮን የሚባዛ ዉጤት የሚያስገኝ ነዉ።

ፍጡር የሆነ ሁሉ በዚች ምድር ዘልዓለም የሚኖር የለም በተለያዩ ምክንያት ያልፋል በእርጅናዉ ወይም በወጣትነት እድሜ ላይ እያለ ። ኢሕአፓ አረጀ መራመድ አቅቶታል እያሉ ይሳለቃሉ ምነዉ ልጅ ወልዶ መተካቱ አያዉቁም ልበል። በዓላማዉ ፀንቶ፣በታሪኩ ኮርቶ፣ ለግላዊ ጥቅም ሳይቋምጥና ኢትዮጵያ በአንድነቷ ፀንታ በዉስጧ የሚኖረዉ ሕብረተሰብ ሁሉ መብቱና ነፃነቱ ተከብሮ የሚኖርባት አገር አደርጋለሁ ብሎ በትግል መስመር ላይ እያለ ማርጀት ምንኛ አኩሪ ታሪክ ነዉ። በጣልያን ወረራ ግዜም እነ አቶ ዜናዊ አርበኛዉ ኢትዮጵያዊዉን ለማዳከም ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም አሁን በኢሕአፓ እንደሚደረገዉ የስም ማጥፋት ዘመቻ። የኢሕአፓ አባሎች በእምነታቸዉ እንደፀኑ ልጅ ወልደዉ ተከተዉ አርጅተዉ ማለፋቸዉ ዋ ያለዉ ክብር። ከተገንጣዮችን ከከፋፋዮች ፍርፋሪ እንመፀወት ይሆናል እያሉ ዓይናቸዉ እንደቀላወጠ አርጅተዉ ለሚሞቱስ ምን ዓይነት ስም ይሰጣቸዉ ይሆን>

**አፉ እንደከፈተ ሳይዘጋ በጣም**
**እንዳማረዉ ሞተ የወያኔ ሆዳም።**

አቶ እያሱ ከሁሉም የበለጠ የሾለ ብእር ስላላቸዉና በሕይወት ስላሉ ራሳቸዉ መከላከል ይችላሉ። እኔም ለረጅም አመታት የተጓዝኩበት ጎዳና በመሆኑ ድርጅቱን አስመልክቶ በሰጡት መልስና አስተያየት ታሪክን ዋቢ በማድረግ ከልብ እጋራዉ አለሁ። ሃሳብን ከሃሳብ ጋር አወዳድሮ ማሳመን ችሎታ የለለዉ ደካማ የሆነ ሰዉ አፉ ያመጣለት ቃል በባእድ ቋንቋ ፅፎ ስላቀረበ ከእኔ በላይ አዋቂ ላሳር ብሎ በሚፅፍ ግለሰብ ማርና ወተት ያቀርብልናል ብሎ ማሰብ ደካማነት ነዉ ። እንዲህ አይነቶቹ ፖለቲካዊ ብስለት የማይታይባቸዉ ስለ ሰፊዉ ሕብረተሰብ ጥቅሙና ጉዳቱ ተረድተዉ የሚጓዙ ሳይሆን ጠባብ አመለካከት ባልበሰለዉ አዕምሮአቸዉ ቀደም ብሎ ገብቶ ስላደናገራቸዉ ጥላቻና የስድብ ሃይለቃል እንጅ በምንም አይነት ገንቢ ትምህርታዊ ትንታኔ እንድንቀስም አያደርጉም። እንግዲህ አቶ **ሮዛ** በባእድ ቋንቋ በመጻፋቸዉ ኩራት መስሎ ካልታያቸዉ በቀር ሌላዉ ዉሃ ቅዳ ዉሃ መልስ ነዉ ጠቃሚ አላየሁበት።

አቶ ሮዛ ብዙ ቅርብ ዘመዶቻቸዉ ከኢሕአፓ ጋር ተሰልፈዉ እንደ ታሰሩና እንደተገረፉ ብሎም

ዉድ ሕይወታቸዉ እንደ ገበሩ ገልፀዋል መኩራትና መንጠራራት ይገባዎት ነበር እንጅ ስማቸዉን ለሚያጎድፍ እበላ ባይ ሁሉ አሳልፈዉ መስጠቱ የእናት ሆድ ዝንጉርጉር ስለሆነ ነዉ ። ባይሆን ኑሮማ የጀግኖቹ ወንድሞችዎ አርማ ተረካቢዉ እርስዎ ነበሩ። ወንድም አቶ ሮዛ የተሰማዎትን ቅሬታ አግባብ ባለዉ መንገድ ራስዎ ያዩት በማስረጃ የተደገፈ ታማኝነት ያለዉ ታሪክ አስተምረዉን ቢሆን ኑሮ እሰይ ይበርቱ መልካም ስራ ባልኩ ነበር። እነዝያ ጀግኖች ወንድሞችዎ ለጠባብ አላማ ሳይሆን ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሉ ለወደቁት አጋር ያልሆኑ ለሌላ ይሆናሉ ብየ አልገምትም። ከሽረኛ ተሳዳቢነት ተላቀዉ ለሞያ አስተማሪነት እንዲበቁ ፈጣሪያችን ይርዳዎት። ያም የሚሆነዉ ብቃቱ ኳሎት ማለቴ ነዉ። ለነገሩ ከፅሁፍዎ እንደተረዳሁት በሳልነት ወይም ጭምተኝነት ሳይሆን በል ተብለዉ ያደረጉት ጉዳይ ስለሆነ ኳለብዎት ተፅእኖ ተላቀዉ  የግልዎ ሃሳብ ተች ለመሆን ያብቃዎት።  ኢሕአፓ የሚወቀስና የሚሰደብ ድርጅት አይደለም ኢትዮጵያን መቶ እጅ ወክሎ የሚታገል ድርጅት እሱ ብቻ ነዉ ። ሌላዉ ሁሉ የብር ምልክት ሲያሳዩት አቅጣጫዉ የሚስት ነዉ።

ይድረስ ለአገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ አገራችን ከሞት አፋፍ ላይ መሆኗ የማያዉቅ ዜጋ ይኖራል ብዬ አልገምትም። ስለዚህ ሰልፋችን አስተካክለን ያሉን ልዩነቶች አጥብበን በአንድነት ተደራጅተን የሚጠበቅብን ድርሻ መወጣት ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆን አለበት ። አለበለዝያ የጥፋት ሃይሎች አሰፍስፈዉ ሊያጠፉን ተነስተዋል።

ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኑር።